# ጋዜጣዊ መግለጫ

አሜሪካ ኤምባሲ

አዲስ አበባ ለተጨማሪ መረጃ በ 011-130-7033 ይደውሉ

2013/16 ድረ ገጽ፡ http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ መንግሥት የግብርና ምርታማነትን ለማሻሻል የሚያስችል አዲስ የመሬት አስተዳደር ፕሮግራም ይፋ አደረገ

ሰኔ 20 ቀን 2005 ዓ.ም. አዲስ አበባ ፡- ክቡር አቶ ስለሺ ጌታሁን የግብርና ሚንስትር ዴኤታ እና ዴኒስ ዌለር የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ኢትዮጵያ ዳይሬክተር “የመሬት አስተዳደር ለልማት መኀልበት ” የተሰኘ አዲስ ፕሮግራም በዛሬው ዕለት በአዲስ አበባ ይፋ አደረጉ፡፡ ይህ ፕሮግራም ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ከዚህ ቀደም የጀመራቸውን ፕሮጀክቶች የሚያጠናክር ሲሆን " ተጨማሪ ክልሎችንም ያካትታል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር እና ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ እ.ኤ.አ ከ2005-2013 በጋራ ተግባራዊ ያደረ[1]ቸው ፕሮጀክቶች" በጂ አይ ኤስ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመሬት አጠቃቀም " የመሬት ባለቤትነት ማስረጃ አሰጣጥና የመሬት ህግ አወጣጥ እንዲሁም በመሬት ሳቢያ የሚነሱ ውዝግቦችን በአካባቢያዊ ሥርዓት ዕልባት የሚያገኙበትን አሰራር አስመልክቶ የተሻለ ግልጽነትን በማስፈን ረገድ በተመረጡ የሙከራ ክልሎች የሚገኙ ገበሬዎችን ተጠቃሚ አድር[1]G፡፡ በውጤቱም ገበሬዎች ሴቶችንና አምራቾችን ጨምሮ በይዞታቸው ሥር ባለ መሬት ላይ ይበልጥ ኢንቨስት አድርገዋል" ምርታማነትም ጨም[ል፡፡ አዲሱ “የመሬት አስተዳደር ለልማት መኀልበት” ውጥን ከዚህ ቀደም ተግባራዊ ከተደረጉ ሁለት ፕሮጀክቶች የተገኙ ተመክሮዎችንና ስኬቶችን መሰረት ያደረገ ሲሆን " በአማራ " አፋር " ኦሮሚያ" ትግራይ "ሶማሌ እንዲሁም በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልሎች ላይ ትኩረት ያድርጋል፡፡

በተጠቀሱት ስድስት ክልሎች ያለውን የመሬት አስተዳደር " አሰራርና ፖሊሲዎች ለማጠናከር" የግብርና ሚኒስቴርና የመሬት አስተዳደር ለልማት መኀልበት ፕሮጀክት ባለሙያዎች ከኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ድርጅት ከክልሎቹ የገጠር መሬት አስተዳደር ኤጀንሲዎች ጋር በቅንጅት ይሰራሉ፡፡ ሦስቱ የተኩረት አቅጣጫዎችም (1) የመሬት ይዞታና የንብረት ባለቤትነትን የሚመለከቱ የህግና የቁጥጥር ማዕቀፎችን ማሻሻል" የዳኞችን ክህሎት ማሳደግ እንዲሁም የመሬት አስተዳደርን የተመለከት የትምህርት ፕሮግራም ማስፋፋት (2) የመሬት አጠቃቀም " የሊዝ ሥርዓት " የውዝግብ አፈታትና የክልል የቅየሳ ባለሙያዎች ስልጠናን ጨምሮ አጠቃላይ የመሬት አስተዳደርን ማጠናከር (3) እንዲሁም የገበያ ትስስርን ለማሳደግ ፣ ንብረት ለማፍራትና የቤተሰብን ኑሮ ለማሻሻል" የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር ማኀበረሰቦችን ውኃ አጠቃቀም ጨምሮ የወል የመሬት አስተዳደርንና የመጠቀም መብትን ማጠናከር፡፡

ፕሮጀክቱ የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅና የገጠር ወጣቶችና ሴቶችን ፍትሃዊ የመሬት ተጠቃሚ ለማድረግ የወጡ ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን ያሻሽላል፡፡ የዚህ ግብ መሳካት ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ኮሚቴ ለዓለም የምግብ ዋስትና ያወጣውን “በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአሳና የደን ይዞታ አጠባበቅ መመሪያ” ተግባራዊ እንድታደርግ እገዛ ያደርጋል፡፡

የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ኢትዮጵያ ዳይሬክትር ዴኒስ ዌለር የመሬት አጠቃቀም ያለውን ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ በተመለከተ ሲያብራሩ “ ግልጽና  በደንብ የታቀደ የመሬት አስተዳደር በምግብ ምርት መዋዕለ ንዋይ ለማፍሰስ" በግብርናው ዘርፍ የተመጣጠነ ዕድገት እንዲኖር " ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንዲሁም በስፋት በገጠር ለሚኖሩና ለሚሰሩ ሴቶችና ወንዶች ሠላምና ዕድገት ወሳኝ ነው” በማለት ተናግረዋል፡፡

የመሬት አስተዳደር ልልማት መጎልበት ፕሮጀክት በአሜሪካው ፕሬዚዳንት መጨውን ትውልድ መመገብ አማካኝነት በቴትራ-ቴክ አሶሽየትስ ኢን ሩራል ዲቨሎፐመንት ከአገር ውስጥ አጋሮች ጋር በመተባበር የሚተገበር ነው፡፡ ሀሮማያና ባህር ዳር የኒቨርስቲዎች በጥምረቱ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ፕሮጅክቱ 11 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚጠይቅ ይገመታል፡፡

###